ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በጥቅምት 8 ቀን 2010 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## ቀዳዳዋ ጀልባ ስትሰምጥ ፤ ተሳፋሪዎቿ ይሸሿታል !

የማነኛውም ሥርዓት፤ በሥልጣን የመቆየቱ ሰዓት ሲያከትም ፤ አባላቱና ደጋፊዎቹ እየጣሉት በየአቅጣጫቸው ይኮበልላሉ። ይኸ ከስተት ትላንት በደርግም ማከተሚያ ወቅት ታይቷል። የቴዎድሮስን ፈልግ እንከተላልን ሲሉ የነበሩት ሁሉ ሳይቀሩ ፤ በፍረሃት ሀገሪቱን እየከዱ ፤ ሕዝቡንም ለሌላ መከራ እያጋለጡ በአሳፋሪ መልከ ኮብልለዋል። **" ብልኽ አይጦች፤ መርከቧ መስጥሰጥም ስትጀምር፤ ወደ ባህሩ ይዘላሉ "** እንደሚባለው ፤ ዛሬም ያ ክስተት እየተደገመ በመሄድ ላይ ይገኛል ። የወያኔ ጋሻ ጃግሬዎችና የወንጀሉ ተባባሪዎች ሁሉ ፤ አንድ በአንድ በየአቅጣጫቸው እየኮበለሉ ናቸው። " ዐይተነው ጊዜ ፤ ወደ አደላበት " በሚለው የጥቅመኞች / የእበላ ባዮች መመሪያ መሠረት፤የነገ ሠልፋቸውን ለማሳመር ፤ ሽሽታቸውን ተያይዘውታል። **"ከሞትና ከአማሪካ ማንም አይቀርም "** በማለት በርካታዎቹ ወደ አማሪካ በማቅናት ላይ እንዳሉ ፤የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ቆይቷል ።

ሀገራችን የመከራ ዘመን ሲያጋጥማት ፤ መሪዎቿና በዝባዦቿ፤ እየጣሏት እንደሚኮበልሉ የቅርቡ አንገት- አስደፊ ታሪካችን መዝግቦታል ። የትላንት በስቲያው፤ ወደ ሎንዶን፤ የትላንቱ ደግሞ ወደ ዝምቧቤ/ ሀረሪ ተጉዘዋል። የዛሪዎቹም ወዴት እንደ ሚኮበልሉ ራሳቸው ወያኔዎቹ አስቀድመው አውቀውታል ። ይብላኝ እንጅ፤ የሀገራችን ሕዝብ ፤ መሄጃ መድረሻ ለሌለው !

ሰሞኑን ቱባ ቱባ የሆኑ የወያኔ ባልስልጣናትና የሕዝብ ሀብት ዘራፊዎች አንድ በአንድ እየኮበለሉና ሌሎቹም ከሥርዓቱ ሹመታቸው እየሸሹና የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ እያስገቡ እንደሆነ የመገናኛ ብዙሃን መረባረቢያ ሆኖ ቆይቷል ። ለስብሰባ ወደ ውጭ ሄደው ከቀሩት መካከል፤ በሥርዓቱ ወታደራዊና የሲቭል መርጃ መዋቅሮች ውስጥ ሁነኛ ቦታ የነበራቸው እንደነበሩ ታውቋል ። ብዙ ምሥጥሮችና የመረጃ ስንክሳሮች ይዘው እንደወጡ ይነገራል ። የያዙትን ሀገራዊ ምሥጢር ፤ ለሚያስጠጓቸው ባዕዳን መንግሥታት፤ የእጅ -መንሻ በማቅረብ፤ የተደላደለ ኑሮ የሚያገኙበት ዋስትና ለማግኘት ተስፋ ያደርጋሉ ። መርኅና ኅሊና የሚባል ነገር ቀድሞውኑም ስለአልተፈጠረላቸው፤ ከወያኔ ጋሻጃግሬነት ወደ ባዕዳን አገልጋይነታቸው ለመንበርከክ፤ የሚያደርጉት ሽሽት፤ ከብርሃን የበለጠ ፍጥነት መኖሩ ያስደምማል ።

ሁሉም ነገር ፤ " **ሲያልቅ አያምር** " ነውና፤ የዘረኛው የወያኔ ግበዐተ- መሬት ሲቃረብ፤ ከአገዛዙ ጋር፤ አባሪ ተባባሪ ሆነው አስረሽ - ምቸው ሲሉ የነበሩ ሁሉ፤ የወያኔን ሬሳ ዐፈር ከማልበሳቸው አስቀድመው እየከዱት የሚከበልልትን አገልጋዮቹን ስንመለከት፤ ይች ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገራችን ፤ምን ዐይነት ኅሊና ቢሶች ፍጡራን እንደሚገዟት አመልካች ሆኗል ። በሌላ በኩል ደግሞ፤ የተያዘ- የተረዘዘው ሁሉ ከሚመጣበት ሕዝባዊ ፍርድ ለማምለጥ የቱን ያኅል በተጠንቀቅ ላይ እንዳለ ያረጋግጣል ። ሀገራዊ ወንጀል የፈፀሙ ሁሉ ፤ ሕዝባዊ ፍርድ እንደሚጠብቃቸው አስቀድመው ከመገንዘባቸው የተነሳ ፤ ዛሬ ሁሉም በየአቅጣቻው ነፍሴ አውጭኝ እያሉ ይኮበልላሉ። የሰሞኑ የሥርዓቱ ቀንደኛ አገልጋዮች መክዳትና

የአንዳንዶቹም የሥራ መልቀቂያ ማመልከቻ ማቅረብ ፤ የሃያ ሰባት ዓመታት ወንጀላቸው ፅዋ ሞልቶ እየፈሰሰ መምጣቱን አመልካች ነው።

የአገዛዙ ቁንጮ ከሆኑት መካከል አንዳንዶች ሰሞኑን፤ በህክምና እያሳሰቡ፤ ቤተሰቦቻቸውን እያያዙ ፤ ወደ ምዕራቡ ሀገራት በመሄድ ላይ መሆናቸው አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ ። በኢትዮጵያ ሰማይ የሚያንዣብበው የለውጥ ወገጋን ፤ ለእነርሱ ፅልመተ-ፍዳ የሚያስከትልባቸው መሆኑን ፤ ማንም ሳይነግራቸው ራሳቸው ደርሰውበታል ። ትላንት ፤ የደርግ ቁንጮ የነበረው፤ ሰማይ-ምድሩ ሲደፋበት ፤ ሀገሪቱንና ሕዝቧ፤ " **ሞኞችሁን ፈልጉ** " ብሎ እንደፈረጠጠው ሁሉ፤ የዛሬዎቹም ካሃድያን ያንኑ ቢደግሙ፤ አሳከርምም። ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ግን፤ የቅርብ ጊዜ የሀገሪቱ መሪዎች ነን ባዮች ሁሉ፤ የሀገር ክኅደት በተከታታይ እየፈፀሙ መቀጠላቸው ነው።

ይኸ ከስተት ለአንዴየና ለመጨረሻው ጊዜ ሊያከትም የሚችለው፤በሕዝቡ በጎ ፈቃድና ሙሉ ተሳትፎ የሚመሠረት ዴሞክራሲያዊ ሥር ዓተ መንግሥት ሲመጣ ብቻ ነው። ያ ደግሞ፤ በምኞትና መፈክር በማስተጋባት ብቻ የሚመጣ አይደለም። ያገባኛል የሚለው ሁሉ ተባብሮና ተስማምቶ የሚያስገኘው ውጤት ነው። ያም ሆኖ ግን፤ ዞሮዞሮ ፤ በዚህም ተባለ በዚያ፤ በሀገራችን የህግ የበላይነት እስካልተረጋገጠ ድረስ ፤ ሁሉም ነገር ከንቱ ነው ። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት መረጋገጫው፤ **የህግ ልዕዋላዊነት ዋስትና ሲያገኝ** መሆኑ ሊያከራክር አይችልም።

ወቅታዊው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፤ በሁሉም ማዕዘናት የሕዝቡ አልገዛም ባይነት በአሻፈረኝነት ታጅቦ መቀጠሉን ያሳያል። ይኸም ሁኔታ፤ ለሀገሪቱና ሕዝቧ የብሩኅ ተስፋ ሰጭ እየሆነ መምጣቱ ግለጽ ቢሆንም፤ ተስፋውን ዕውን ለማድረግ ግን፤ ሀገር -አቀፍ ትግሉን እያፋፋሙ መቀጠል አማራጭ አይኖረውም ። ሕዝባዊ አመፁን በቀጣይነት ማፋፋም እንጅ፤ ትግሉን፤ ቦግ -እልም በሚል ሁኔታ ማስተናገድ፤ የወያኔን ዕድሜ ከመቀጠል በቀር ሌላ ርብና አያመጣም። በአንጻሩ ግን የሕዝቡን ተስፋ የማጨልም ተፅዕኖ ይኖረዋል ። ይኸ በበኩሉ፤ ለወያኔ የልብ- ልብ ይሰጠዋል። ይኸ ግን ለዘለቄታው የሚቆይ አይሆንም። ምክንያቱም፤ ምን ጊዜም ቢሆን፤ የመጨረሻው አቸናፊ የምልዐተ- ሕዝብ ትግል መሆኑ የማይቀር ስለሆነ ነው።

ትላንት ዕዩኝ ዕዩኝ በማለት፤ ማንም አይደፍረንም ሲሉ ለነበሩት ዘረኞችና ተባባሪዎቻቸው ግን የሞት ፅዋ የሚጋቱበት ጊዜ እንደሆነ አውቀውታል ። ሀገር አጥፍተው ፤ ሕዝብ በታትነውና ታሪክ ደምስሰው፤ የራሳቸውን እኩይ አጀንዳ ለማስፈፀም ላለፉት ሃያ ሰባት ዐመታት ሲዳከሩ የነበሩት ሁሉ፤ የማታ ማታ ማንም አዳኝ እንደማያገኙ የዐለም ፖለቲካ ያረጋግጣል ። የዐለም ሀገሮች እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ችግሮች ለመወጣት በሚጥሩበት በአሁኑ ወቅት፤ ስለሌላው ሀገር ችግር ደንታ ሊኖርቸው አይችልም። በመሆኑም፤ ወያኔ ከገባበት ማጥ ማንም ኃይል ሊያወጣው እንደማይችል የተረጋገጠ ነው። በወቅቱ የዐለም ፖለቲካ ይዘትና አካሄድ፤ ማነኛው ሀገር " **የራሱ እያረረበት ለሌላው የሚያማስልበት** " ጊዜም ሆነ ትኩረት፤ ደንታም ሆነ አቅም ሊኖረው አይችልም። ሁሉም ሀገራት ቅድሚያና ትኩረት የሚሰጡት ፤ ስለ ሀገሮቻቸው ብሄራዊ ጥቅምና ስለ ዜጎቻቸው ደህንነትና ሠላም እንጅ፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን ትኑር አትኑር፤ ሠላም ይኑራት አይኑራት፤ ትበተን፤ አትበታተን ጉዳያቸው አይደለም ።

ኢትዮጵያ ከገጠማት ችግር መውጣት ይኖርባታል ከተባለ፤ ሊያወጧት የሚችሉት የራሷ ልጆች ብቻ ናቸው። ይኸ ደግሞ በታሪክ የተመሰከረለት ሃቅ ነው። እያንዳንዱ ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፤ ይኼንን ይስተዋል ማለት አይቻልም። ይኸም ስለተባለ ግን ፤ ሀገሪቱ ከገባችበት አደጋ ለማውጣ፤ ሁሉም የሚጠበቅበት እያደረገ ነው ለማለት ከቶ አይቻልም። ሁሉ ተባብሮ የሚጠበቅበትን ቢያደርግ ኖሮ፤ ወያኔ ግማሽ ምዕተ- ዐመት በሥልጣን መቆየት አይችልም ነበር ። የተባበረ ሕዝባዊ አመፅ፤ ለአንድ ቀን ዠምበርም ቢሆን ለመቆየት ዕድል እንደማይሰጠው ያውቀዋል። አምባገነኖች በሥልጣናቸው ለመቆየት፤ የ " ከፋፍለህ ግዛ" ዘዴ መጠቀማቸው የቆየ ቢሆንም፤ ወያኔ ግን ሕዝብን በቋንቋና በዘር መከፋፍሉ ብቻ ሳይሆን፤ ዜጎችን እያደኸዩ፤ እያደነቆሩ፤ ቅስም እየሰበሩ፤ እያስራቡ፤ መንፈሳቸውን እያዋረዱ፤ እያሰሩ፤ እየገደሉ፤ ከሀገር እያሳደዳና ሌሎቹንም ተዘርዝረው የማያልቁ ወንጀሎችን ሁሉ እየፈፀመ እስካሁን አለ። አደገኞች ናቸው ብሎ በሚፈራቸው ብሄሮች ላይም ዐይን ያወጣ የዘር ማጥፋት (Genocide ) ወንጀል እየፈፀመባቸው ይገኛል።

የሰውን ዘር ማጥፋት፤ የአምባገነኖችን ችግር እሚፈታው ቢሆን ኖሮ፤ የናዚዎች ዕቅድ ዐላማውን በመታ ነበር። ያ ግን ሊሳካ አልቻለም። የስድስት ሚሊዮን አይሁዶች መጥፋት ፤ ዞሮ ዞሮ ችግር ያስከተለው፤ በወንጀሉ ተባባሪ ባልነበረው በጀርመን ምልዐተ- ሕዝብ ላይ ነው። ለሰብዐዊ ፍጡር ሁሉ ፤ የኅሊና ቁስልን ትቶ አልፏል ። የወያኔ ወንጀል፤ ግን በብዙኃኑ የትግራይ ሕዝብ ዘንድ አስተጋብዖ የኖረዋል ብሎ ማለት አይቻልም። ይኸ ዕውነታ እንዳለ ሆኖ፤በስሙ ወንጀል የሚፈፀምበት ትግራዋይ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ፤ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር በመተባበር፤ ሀገሩ ከገባችበት አደገኛ ሁኔታ ለማውጣት በሚደረገው ሀገራዊ ትግል ፤ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጥሪው ይተላለፍለታል ። ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጎቿ ሀገር ነች እስከተባለ ድረስ፤ ህይወቷን ለማትረፍ ሁሉም የሚጠበቅበትን ህብረተ--ሱታፌ ማድረግ ግዴታ ይሆናል ።

ብሩኅ ተስፋ ያላትን ፤ የነገውን ኢትዮጵያ ለመመስረት፤ ዛሬ ሁሉም ዜጋ የበኩልን ድርሻ መወጣት፤ መብትና ግዴታ፤ ተልዕኮና ኃላፊነት እንዳለው ሊያውቀው ይገባል ። የጋራ ሀገርን አድኖ፤ በጋራ ብልፅግና ላይ ለማተኮር ከተፈልገ፤ መዳኅኒቱ በጋራ መቆም ነው። የወያኔ ባለሥልጣናት መሸሻቸውን ይቀጥላሉ። ዕውነተኛ ዜጎቿም ሀገራቸውን ለማዳን ይታገላሉ። ካዳኗትም በኋላ፤ እያለሙ ያበለፅጓታል፤ ያፋፏታል፤ ያጠንክሯታልም ! የዚኽ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ፤ ነፃነቷ የተጠበቀ አንዲት ኢትዮጵያ በዘለዓለማዊ መልኳ እንድትቀጥል ዋስትና ይሰጣል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን፤ የሁለት ስትራተጂያዊ ሀብቶች ባለቤት ነች ። እነርሱም፡-

**1ኛ.** የዐባይ ምንጭ መፍለቂያ **2ኛ.** የአፍሪካ ቀንድን ለመቆጣጠር፤ በተፈጥሮ ፀጋ የታደለች መሆኗ ናቸው። ሁለቱንም በአግባቡ መጠቀም ከቻለች ፤ የነፃነቷንና የደኅነቷን ዋስትና ታረጋግጣለች ። ለዚኽ ስትራተጂያዊ ራዕይዋ መረጋገጫ ዋስትና የሚሆናት ግን ፤ በዴሞክራሲ ሥርዓት የሚተዳደር ሕዝብ ሲኖራት የሆናል ።የጠነከረች ሀገር ለመሆን የሚያስችላት ዐብነቱ፤ መብትና ነፃነቱን አስከብሮ የራሱ ገዥና ተገዥ ሕዝብ ያላት መሆኗን ስታስመሰክር ነው።

የ1966 ዓም የካቲት ዐብዮት ታሪካዊነቱ ፤ ከአያሌ ዘመናት በኋላ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዥዎቹን ራሱ መለወጥ ማስቻሉ ነበር ። ነገር ግን፤ የመከራ ገመዱ ስለአልተቆረጠለ፤ ያ ታሪካዊ ድሉ፤ በወታደር አምባገነን ቡድኖች ስለተነጠቀ፤ የራሱ ገዥ ሳይሆን ቀረ። ያ የየካቲት አመፅ አሁንም በሌላ መልኩ በሀገራችን የፖለቲካ አድማስ እያንዣበበ ነው ። ድሉን ለመንጠቅ ዛሬም እንደ ትላንቱ አስፍስፈው የሚጠባበቁ ነጣቂ ኃይሎች ተዘጋጅተው አድፍጠዋል።

እነርሱን ተከላክሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ድል ለሕጋዊ ባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስረከብ ፤ የዕውነተኞቹ ታጋይ ኢትዮጵያውያን ኃላፊነት እንደሆነ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። አንድ ሕዝብ በህይወቱ ሊታለል የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ መሆን አለበት።

ሀገራችን " **ኢትዮጵያዊ ሆኜ ባልወለድ ኖሮ ፤ ኢትዮጵያዊ መሆንን እመርጥ ነበር** " የሚል ዜጋ እንዲኖራት ያስፈልጋል ።

ጀልባው ተስጥማለች ። ተሳፋሪዎቿም ጥለዋት እየሸሹ ናቸው ። ሀገራችን ግን በነፃነት መኖሯን ተቀጥላለች ።

ሊያጠፏት የከጀሉ ሁሉ ግን ጠፍተው ይቀራሉ !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች!